Amhara Association of Oregon

https://oregonamhara.org/

Email: contact@oregonamhara.org | Phone: 971-429-8801

# አንድ የመሆን ጊዜው አሁን ነው።

የአማራ ህዝብ በተለያዩ ምክንያቶች ሀገሩን በመተው በስደት በመኖር እና በኑሮውም ውጤታማ በመሆን ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወንድምና እህቶቹ ቀዳሚ ሳይሆን አይቀርም ተብሎ ይታመናል። በስራዎቹም አንቱ የተባለና የተከበረ ህዝብ ነው። በአንድነት በመሰባሰብ ለአማራ ህዝብ የበለጠ አስተዋጽኦ ለማድረግ በማህበር ተሰባስቦ በርካታ አስተዋጽኦችን እያበረከተ መሆኑ የሚታወቅ ጉዳይ ነው። በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ አደጋዎች በተለያየ ጊዜ አደጋ ለደረሰባቸው ወገኖቻችን በማህበሩ አሰባሳቢነት በርካታ ድጋፎችን እያደረገ መገኘቱም ለህዝቡና ለሰብአዊነት ያለውን ልዕልና ያሳያል። በቅርቡም በአማራ ህዝብ ላይ በተቀናጀ መልኩ እየደረሰ ባለው የዘር ማጥፋት፣ መፈናቀልና ስደት ምክንያት የአማራ ህልውና ለማረጋገጥ ነፍጥ ያነሱ ፋኖዎቻችንን ለመደገፍ በማህበሩ በኩልም ሆነ በግልም ደረጃ አስተዋጽኦ በማድረግ የህልውና ትግል ዳር እንዲደርስ እየተሰራ መሆኑ ያስመሰግናል። እንዳለ መታደል ሆኖ ሀገር መንግስት ባጸና፣ ፍትህን በሀገር ደረጃ ባስተማረ፣ የስልጣኔ መሰረት ሆኖ የስልጣኔ ቀንዲልና ፍኖት በሆነ፣ የሀገርን ነጻነት ባጸና፣ በዛሬ ተረኞች በናዚ ዘመን እንኳን ያልተፈጸመ ግፍ እንዲቀበል ተደርጓል። የደረሰውን ግፍ በመዘርዘር ለቀባሪው እንደማርዳት ስለሚሆን እንተወዋለን። የምናደርገው እርዳታ ለልማት ቢሆን ኑሮ ስንት ወገኖቻችንን ከድህነት ባወጣን ነበር። የሆነው ሆኖ የአማራ ህዝብ የተፈረደበት ጦርነት፣ ስደት፣ መፈናቀልና የዘር ጭፍጨፋ ስለሆነ ድጋፋችን በዚሁ የተቃኘ መሆኑ አይቀርም ህልውናውን አስጠብቆ ወደ ልማት እስኪገባ ድረስ።

ከላይ ያለውን ሃልዮ ስንመለከት የአማራ ህዝብ በአንድነት ሊሰራቸውና ሊወጣቸው የሚገቡ በርካታ የቤት ሥራዎች እንዳለበት መገንዘብ ይቻላል። የሚያስገርመው ነገር ደግሞ እነዚህ የቤት ስራዎች በሙሉ ከእሱ የመጡ ሳይሆኑ በተለይም ካለፉት 50 ዓመታት ጀምሮ በተፈራረቁ መንግስታት አቀናባሪነት እንደ ኮሶ እንዲጠጣው የተሰጡት ናቸው። የአሁኑ ትውልድ ደግሞ ይህ ግፍ ይብቃ ብሎ ህይወቱን ለአማራ ህዝብ ለመስጠት እየተዋደቀ ይገኛል። ከሞቀ ቀያቸው አፈናቅሎ ያለመጠለያ ያስቀራቸው መንግስት በላስቲክ ድንኳን መጠለያ ያሉ ወገኖቻችንም በርሃብ በርሃብ እያለቁ ነው። የክልሉ ወጣቶችም በድንቁርና እንዲኖሩ ተፈርዶባቸዋል።

እነዚህን ዘርፈ ብዙ ችግሮችን በመያዝ በኦሪገን የአማራ ልማት ማህበር ከ2024 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) ጀምሮ በርካታ አዎንታዊ እንቅስቃሴዎችን እያደረገ ይገኛል። አሁንም ይህንን አጠናክሮ መቀጠል ይፈልጋል። ይሁን እንጂ አንድ ውጤታማ እርምጃ መራመድ የሚቻለው በኦሪገን የምንኖር አማራውያን በጋራ መንቀሳቀስ ስንችል መሆኑን የማህበሩ አመራር በጽኑ ያምናል። በዚህ በሰለጠነው ዓለም ብንኖርም ልባችን ያለው ከህዝባችን ጋር ስለሆነ ያልተቋጨውን የአማራ ህልውና የማስጠበቅ ጉዞን በጋራ በመሆን አስተዋጽኦ ማድረግ እንዳለብን እናምናለን። ጊዜ፣ ገንዘብ፣ የእውቀትና የቁሳቁስ አስተዋጽኦ ህልውናውን እየሰጠ ካለው ህዝባችን በላይ ነው ብለንም አናምንም። በዓለም ላይ የተደረጉ የነጻነት ትግሎች እልህ አስጨራሽና ዘመን ተሻጋሪ ናቸው። ደንበር ተሻጋሪም ናቸው። ቼ ጎቤራ የተባለ አርጀንቲናዊ ለኩባ መዋደቁን ስናስብ እኛስ ከአብራኩ ለወጣነው ህዝብ ምን እናድረግ ብለን ማሰባችን ግድ ነው። እስራኤላውያንንም መውሰድ እንችላለን። ለአንድ ጠንካራ ጽዮናዊት ሀገር በገሃድም ሆነ በህቡዕ የሚያደርጉት አስተዋጽኦን እንደተምሳሌት መውሰድ ይቻላል። እኛስ ለህዝባችን ህልውና እንደነሱ ሙሉ በሙሉ ባንሆን ጥቂቱን መሆን እንዴት ያቅተናል ብለን እንዲቆጨን ያደርጋሉ። በመሆኑም ይህን የህልውና እንቅስቃሴ ባለን አቅም ሁሉ መደገፍ ለነገ የሚባል ነው ብለን አናስብም። ማህበሩ በዚህ መንፈስ ወደፊት አጠናክሮ መቀጠል ይፈልጋል።

ግልጽ መሆን ያለበት ድጋፍ ሲባል በገንዘብ ብቻ አይደለም፤በእውቀትና በቁሳቁስ እርዳታም ሊሆን ይችላል። ከሁሉም በላይ ደግሞ በአንድነት በመሰባሰብ በአለንበት ግዛት ላሉ ባለስልጣናት በህዛባችን ላይ እየደረሰ ያለውን ግፍ የበለጠ ግንዛቤ እንዲያገኙ መስራት ትልቅ አስተዋጽኦ ማድረግ ነው። በግልም ስለአማራ ግፍ በአገኘነው አጋጣሚ ሁሉ የዲፕሎማሲ ስራ መስራት ያስፈልጋል። ይህ ደግሞ ከቦታው ላሉት ብቻ ሳይሆን ከሞት አምልጠው እየተሰደዱ ለሚመጡ ወገኖቻችንን ስቃይ መንግስታት እንዲረዱ በእጅጉ ይረዳል። በዚህ ዙሪያ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ድርጅቶች የሰሩት ስራን እንደመልካም ተሞክሮ መውሰድ ያስፈልጋል። ሌላው የአማራ ህዝብ በመንታ መንገድ ላይ ነው ያለው ብሎ ማህበሩ ያምናል። አንደኛ የተጀመረውን የህልውና ትግል በአሸናፊነት መወጣትና ህዝባችን ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር ፍትሃዊ በሆነ እኩልነት አንገቱን ቀና አድርጎ አብሮ እንዲኖር ማስቻል ወይም ደግሞ ዳር ቁመን ከሌሎች አሸናፊነትን ስንጠብቅ በሽንፈት ከተጠናቀቀ የአማራ ህዝብ ሁሌም አንገቱን ደፍቶ በበለጠ ግድያ፣

በበለጠ መፈናቀል፣ የእሱ የሆኑ እሴቶችን፤ የእምነት ተቋማቱን፣ ባህሉን ወዘተ አጥፍቶ እንደ ኩርድ ማህበረሰብ በሀገሩ ስደተኛ ሁኖ እንዲቀር ይሆናል። በአሸናፊነትም ሆነ በተሸናፊነት ታሪክ ውስጥ የእኛ አስተዋጽኦ ይመዘገባል። ምርጫው አንድ ነው በአሸናፊነት ታሪክ ውስጥ መካተት።

ከ3 ሚሊዮን የማይበለጡ የትግራይ ህዝቦች ኢትዮጵያን በዘር ከፋፍለውም ቢሆን ሀገራችንን የገዙት ህብረት ስለነበራቸው ነው። መከፋፈልና መጠራጠር በተለይ በአማራ ህዝብ አእምሮ ላይ በመንግስት ደረጃ የተሰራ ቢሆንም አሁን የመለያየት አባዜ መጥፋትና እንደ አማራ በአንድነት መስራት ጊዜ የማያሻው ጉዳይ ነው ብሎ ማህበራችን ያምናል። አመራሩም በኦሪገን የምንኖር አማራዎች በአንድነት የምንቆምበት፣ በአንድነት የምንደግፍበትና ለወገኖቻችን በገንዘብ፣ ድምጾቻቸውን ይዘን አለን የምንልበት ጊዜ ነው። እንደ እጅ ጣቶቻችን ልዩነቶች ቢኖሩንም ጣቶቻችን ልዩነትን ትተው ተባብረው ውጤታማ ስራ እንደሚሰሩት ሁሉ እኛም በአንድነት በመንቀሳቀስ ውጤታማ ስራ መስራት ጊዜው የሚጠይቀው ጉዳይ ነው ብለን እናስባለን። ይህ እውን እንዲሆን ደግሞ አመራሩ ከመቸውም ጊዜ በተሻለ አዳዲስ የአሰራር ስልቶችን በመቀየስ ውጤታማ ስራ ለመስራት ዝግጁነት አለው።

ይህ ሁሉ እውን የሚሆነው ግን በአማራ ህዝብ ላይ ከቀደምት አባቶቻችን ዘመን ጀምሮ በቀኝ ግዥ መንግስታት በተጠነሰሰ ሴራና ዛሬ አብሮ ከኖረው ማህበረሰብ በፈለቁ ዜጎቻችን እየደረሰ ያለውን አሰቃቂ እልቂትና የህልውና አደጋ፣ ሁለንተናዊ ችግሮችን በመገንዘብ እኔም በበኩሌ በጎ አስተዋጹኦ ለህዝቤ ላድረግ ብሎ የሚነሳ ህብረተሰብ ሲኖር ነው። በዚህ ደግሞ የኦሪገን ኗሪ የአማራ ህብረተሰብ ያለማቋረጥ የሰራቸው ስራዎች ምስክር ናቸው። ስለዚህ አንድ የመሆን ጊዜው አሁን ነው በማለት በምናደርገው አጠቃላይ ስብሰባ ላይ በመገኘት የበኩላችሁን አስተዋጽኦ እንድታደርጉ ኮሚቴው ጥሪውን ያቀርባል።

አንድ የመሆን ጊዜው አሁን ነው።

የአማራ ማህበር በኦሪገን